# የህዝባዊ ስብሰባ ጥሪ

እናት አገራችን ኢትዮጵያ እጅግ በጣም አሳሳቢና ወሳኝ በሆነ ታሪካዊ ወቅት ላይ ትገኛለች። **የኢትዮጵያ ህዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢህአፓ)**፤ ባንድ በኩል የወያኔ/ኢህአዴግ መንግሥት የህዝባችንን የማይገሥስ መብት ዋንኛ መግለጫ የሆነውን በትረ-መንግሥት በነፍጥ ነጥቆ በሥልጣን ከተቆናጠጠ ጀምሮ የዴሞክራሲያና ፍትህ ተሟጋቾችን እየጨፈጨፈ፤ በእስር ቤት እያጎረና አገራችንም ሰላም እንዳይኖራት በየማዕዘኑ ጠብ እየጫረ በማያባራ ጦርነት ውስጥ እየዘፈቃት በመሆኑ፤ በሌላ በኩል ደግሞ፤ የ **"ካልተባበራችሁ፤ ተሠባበሩ"** እርግማን ያለበት ይመስል በአንድ ግንባር መቆም ያዳግተው የተቃዋሚ ጎራ መኖር፤ እጅግ አሳሳቢና አነጋጋሪ ከሆኑት የወቅቱ ጉዳዮች ውስጥ ሁለቱና ዋነኞቹ ናቸው ብሎ ያምናል። በእነዚህና እነዚህን በመሣሰሉ ጉዳዮች ዙሪያ ከህዝብ ጋር በግንባር ተገናኝቶ መወያየት እጅግ አስፈላጊና አንገብጋቢም ጉዳይ በመሆኑ የኢህአፓ ከፍተኛ አመራር በተለያዩ ሀገሮችና ከተሞች ውይይቶች በማድረግ ላይ ይገኛል።

በሰሜን አሜሪካ ለሚገኙ ወገኖቻችን በተለያዩ ከተሞች በመካሄድ ላይ ያለው ህዝባዊ ስብሰባ አሁን በፒንሴልቫንያና በአጎራባቾች ውስጥ ለሚኖሩ ኢትዮጵያን **በፊላዴልፊያ ከተማ ይደረጋል። ኢህአፓን** በመወከልም የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር አባላት ስለአገራችን ህልውናና የወደፊት አቅጣጫ በጋራ ለመምከር የሚደረገውን ውይይት በግምባር ለመምራት በቦታው ስለሚገኙ፤ ጉዳዩ ለሚመለከታችሁ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ሁሉ የስብሰባው ተካፋይ እንድትሆኑ ጥሪያችንን ብታላቅ አክብሮት አእናስተላልፋለን።

- **ቦታው፦** International House<br>3701 Chester Street
- **ቀኑ ፦** **እሁድ፡** April 1, 2007
- **ሰዓት፦** 2:00 PM — 6:00 PM

**የመስብሰቢያውን አድራሻ ለማግኘት ችግር ከገጠመዎት በ 609-560-8189 ደውለው ያነጋግሩን።**

**በፊላዴልፊያና አካባቢው የኢህአፓ አባላትና ደጋፊዎች**